ለኢትዮጵያ አንድነትና ዴሞክራሲ Unity & Democracy For Ethiopia
የኢትዮጵያ ሕዝብ አርበኞች ግንባር
Ethiopian People's Patriotic Front

July 25, 2006

# ዛሬም እንደ ትናንቱ!!

ከኮማንደር መስከረም አታላይ፥ የኢትዮጵያ ሕዝብ አርበኞች ግንባር ዋና አዛዥና ሊቀ መንበር፥ ለኢትዮጵያ ሕዝብ የሚከተለውን መልዕክትና ጥሪ አስተላልፈዋል፤

## ይድረስ ለመላው የኢትዮጵያ ሕዝብ፡-

በአገራችን በቅሎ የታሪክ አተላ በሆነው በፀረ-ኢትዮጵያው ሕዝባዊ ወያኔ ሐርነት ትግራይ (ወያኔ) የጭፍጨፋ የእስራትና የረሃብ ሰቆቃ ስር ለምትገኘው የኢትዮጵያ ሕዝብ፥ በተለይም ለቤተሰብህ ስትል በማታምንበት የሃገርህ ጠላት በሆነው በወያኔ አመራር ስር በመለዮ ለባሽነት ተቀጥረህ በማገልገል ላይ ለምትገኝ የኢትዮጵያ ሠራዊት በሙሉ፥ ለወጣቱ ትውልድና ለመላው አገር ወዳድ አርሶ አደር በሙሉ፤ አያት ቅድመ አያቶቻችን እንደ መለስ ዜናዊ ከመሳሰሉ የውስጥ ቦርቧሪዎችና የጠላት ምንደኞች (ቅጥረኞች) እንዲሁም ከውጭ ወራሪ ኃይሎች በመከላከል ዳር ደንበሯን ጠብቀው ያቆዩልንን የእናት አገራችን አንድነትና የአንተም የዕለት ከዕለት ህይወት እምን ላይ እንዳለች እናውቃለን። ይሄውም እንደሕዝብነትህ በአገርህ ተቀጥረህ በማገልገል ቤተሰብህን እንዳትመግብ፥ ነጋዴው ነግደህ እንዳትኖር፥ አርሶ አደሩም አርሰህና አምርተህ ልጆችህን እንዳታሳድግ፥ ወጣቱ ትውልድም ተምረህ ዕውቀት በመገብየት አገርህን እንዳትረዳ፥ መለዮ ለባሹም በኢትዮጵያዊነትህና በሥራህ ዋስትና እንዳይኖርህ እርስ በርስህ በማናከስ፥ በአጠቃላይ በገዛ አገርህ በዜግነትህ መብትህን ሳትጠይቅ ተገዥ ሆነህ ለመኖር ብትፈልግ እንኳ ወያኔና ቅጥረኞቹ ብሎም ካድሬዎቹ በሰበብ ባስባቡ የሚያደርሱብህን በደል እኛ የኢትዮጵያ ሕዝብ አርበኞች ግንባር በሚገባ እናውቃለን። ይሁን እንጅ የጊዜ ጉዳይ ነው።

ሁላችሁም እንደምታውቁት የኢትዮጵያ ቀንደኛ ጠላት የሆነው ሕወሐት ከአሁን ቀደም ሆን ብሎ በባድሜ ጦርነት ላይ ከሰባ ሺህ በላይ ወገኖቻችን እዲረግፉ አደረገ፤

በብዙ ሽህ የሚቆጠሩም አካለ ስንኩል ሆነው በየመንገዱና በየቤቴክርስቲያኑ ለልመና ተጋለጡ፡፡ ከሞትና ከአካል ጉዳት ተርፈው የተመለሱትንም እንዲሁ ያለአንዳች መቋቋሚያና ካሣ ከሠራዊቱ አስወጥቶ ስለበተናቸው ቦዘኔና ሥራ አጥ አደረጋቸው፡፡ ኑሮአቸውም ቤተሰባቸውም ፈረሠ ታዳጊ ልጆቻቸው ሁሉ ለርሃብ ለችግር፥ ለበሽታና ለድንቁርና ተጋለጡ፡፡ ወያኔ ግን ይፈራው የነበረው የኢትዮጵያ ሕዝብ ኃይል በጦርነቱ ስለ ተቀነሰለት እፎይ አለ፡፡ ወያኔ ዛሬም እንደትናንቱ በማይመለከትህ ጦርነት ውስጥ ሊማግድህ ነው፤ ወያኔ ባለፈው ዓመት በተደረገው የፓርላማ ምርጫ ባልጠበቀው ሁኔታ በውርደት በመሸነፉና በዓለም ፊትም በመጋለጡ የመሞቻ ጊዜው እንደደረሰ በመገ ንዘብ የምርጫውን ውጤት ሰርቆም ሆነ አጭበርብሮ አሸነፍሁ ለማለት እንደማይችል ሲያውቀው ያሸናፊውን የቅንጅት ፓርቲ መሪዎችና ጉዱን የሚያወጡበትን የኢትዮጵያ ጋዜጠኞች ማህበር አባላትን፥ ወጣቱን ትውልድ፥ አገር ወዳድና ምሁራኑን ሁሉ እስር ቤት አጎረ፡፡

በዚህም ህገወጥና ኢ-ሰባዊ ወንጀሉ ፊትነስቶት የነበረውንና የኢኮኖሚ ልገሳውን ማዕቀብ አድርጎበት የነበረውን የአውሮፓን ህብረተሰብ ስሜት ለመለወጥ እንዲሁም ጌታውንና ሞግዚቱን ለማስደሰት ሲል እነሆ በአሁኑ ወቅት ከኢትዮጵያ ህዝብ ጋር ምንም ዓይነት ጠብ የሌለውን የሶማሌን ህዝብ በመርስነሪነት (በቅጥረኛነት) በመውረር ላይ ይገኛል፡፡ ሁለተኛው የወያኔ የወረራ ስውር ዘዴ፥ በአሁኑ ወቅት በአጠቃላይ የኢትዮጵያ ሕዝብ በመተባበር እየተነሳበት እንደሆነና በተለይም የኢትዮጵያ ህዝብ አርበኞች ግንባር ወያኔን ከመንበሩ አውርዶ ለመጣል ወደፊት በመገስገስ ላይ በመሆኑ ተንኮለኛው ወያኔ ለአገሩ ተቆርቋሪ የሆነውን መለዮ ለባሽ ሠራዊት ወጣቱንና አርሶ አደሩን በማስገደድ ወደ ማይፈለግና የእኛ ባልሆነ ጦርነት ላይ ማግዶ ለማስጨረስ ሲል ዛሬም እንደትናንቱ የሸረበው የተንኮል ጦርነት መሆኑን እንድታውቀው ይሁን፡፡ በአሁኑ ወቅት ወያኔና ባንዳዎች አንተን በማታለል በውሸት ቅስቀሳ ወደ ጦርነቱ እንድትገባ ለማድረግ አክራሪ እስላሞች የክርስቲያኖችን አገር ኢትዮጵያን ሊወሩ ስለሆነ እኛ የኢትዮጵያ ህዝብ መዋጋት አለብን የሚል የሐሰት ቅስቀሳ እያናፈሱ ናቸው፡፡ ይህ ፍፁም ሐሰትና ውሸት ነው፡፡ ሶማሌዎች በአሁኑ ወቅት ኢትዮጵያን ሊወሩ አልተነሱም፡፡ ሶማሌዎች ባሁኑ ወቅት የተነሱት ጭራቁ የወያኔ መሪ መለስ ዜናዊና ጌቶቹ በአገራችን ላይ የነሱን ጥቅም አስከባሪና ትዕዛዝ ፈጻሚ የሆነውን የወያኔን አሻንጉሊት መንግሥት እንዳቋቋሙብን ሁሉ በሱማሌም ምድር ላይ እንዲሁ የሱማሌ አሻንጉሊት መንግሥት ስለፈጠሩባቸው ያንንና መለስ ዜናዊን ለመቋቋም ብሎም ለማፍረስ ሱማሌች የጀሃድ ጦርነት ማወጃቸው ግልፅ

ነው። ወያኔ ግን በዚህ ጦርነት ላይ ለመጠቀም ካቀዳቸው ብዙ የመሠሪ ተንኮሉ ውስጥ ኢትዮጵያዊ መለዮ ለባሹን፥ ወጣቱንና አርሶ አደሩን ለማስጨረስ ጭምር ነው።

ኢትዮጵያ ከነቢዩ መሐመድ ዘመን ጀምሮ የክርስቲያኖችና የእስላሞች አገር መሆኗ የታወቀ ነው። የሁለቱ እምነት ተከታይ የሆኑ ኢትዮጵውያን ተከባብረውና ተዋደው የሚኖሩ አንድ ሕዝብ ናቸው። ስለዚህ አሁንም መሰሪውና ፋሽስቱ የወያኔ መሪ ባጠመደልህ የጦርነት ወጥመድ ውስጥ ተገደህም ቢሆን እንዳትገባ የኢትዮጵያ ህዝብ አርበኞች ግንባር ብሔራዊና ወገናዊ ጥሪውን ያስተላልፍልሃል።

የኢትዮጵያ መለዮ ለባሽ ሠራዊትም የመሣሪያህን አፈሙዝ በሱማሌ ሕዝብ ላይ ሳይሆን ወደ ማን ማዞርና ማነጣጠር እንዳለብህ መገንዘብ ይኖርብሃል። በአጠቃላይ ወጣቱና ገበሬው እንዲሁም መለዮ ባሹም ብትሆን ወደ ጠረፍ ብትመጣ ተቀብለን በማደራጀት በአገራችን ጠላት ላይ ተመልሰህ እንድትዘምት እናደርግህአለን።

በተረፈ ዛሬም እንደትላንቱ (እንደባድሜ) በከንቱ ጦርነት ውስጥ እዳትማገድ በአደራ ጭምር እናሳስባለን።

## ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ ! ሞት ለወያኔና ግብረ አበሮቹ!